EthioLion

ዴሞክራሲያ

የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ልሳን

ዴሞክራሲያ ቅጽ 35 ቁጥር 3 ታኅሣሥ 2002 ዓ.ም

## ታህሣሥ ሲዘከር፤ መስዋዕትነት ሲከበር

በሀገራችን የወራት አቆጣጠር ሰሌዳ የታህሣሥ ወር የሚዘከርበት የታሪክ ምዕራፍ አስመዝግቦ አልፏል፡፡ በዚህ የታሪክ ምዕራፍ ከተጻፉት መሠረታዊ ምንባብ ውስጥ ሁለቱ ዘወትር ተዘክረውና ተከብረው ይኖራሉ፡፡ እነርሱም፥ የለውጥ ፈላጊው ትውልድ የሀገር ፍቅር ስሜትና የኢትዮጵያ ወጣቶች መሥዕዋታዊ ገድል ናቸው፡፡ ሁለቱም በኢትዮጵያ የለውጥ ታሪክ ሁነኛ ቦታ ተሰጥቷቸዋል፡፡ ተተኪው ትውልድም እየዘከራቸውና እያከበራቸው፤ የየራሱን ሀገራዊ ድርሻ እየተወጣ፤ ሀገሩን እየታደገና እያሳደገ ይቀጥላል፡፡

ይህን ታሪካዊ ሐቅ ማንም ሊሽረው፥ ሊበርዘውና ሊሰርዘው አይችልም፡፡ በታሪክ፥ ኢትዮጵያን በኢትዮጵያዊነቷ ታፍራና ተከብራ እንድትቆይ ያደረጓት ሀገር ወዳድ ጀግኖች እንደነበሩ ሁሉ፥ ታሪካዊ ኀልውናዋንና ነፃነቷን ጠብቃ ዘመናዊ ለውጥ ያስፈልጋታል ብሎ የተነሳው ለውጥ ፈላጊው ትውልድም በበኩሉ ሀገራዊ ፍቅሩን የገለጸላት፥ አይከፍሉ መሥዋዕት በመክፈል ነበር፡፡ ይህም ራሱን የቻለ ታሪካዊ ሐቅ በመሆኑ፥ ታሪክ በራዦች ሊበክሉት አይችሉም፡፡ ታሪካዊቷ ሀገራችን ኢትዮጵያ ነፃነቷና አንድነቷ እንደተጠበቀ ሆኖ፥ በዕድገትና በልማት ግን ኋላቀር መሆን የለባትም ብለው የተነሱ ልጆቿ ለውጥ የሚያስፈልጋት መሆኑን አምነው መነሳታቸው በታህሣሥ ወር ለመሥዋዕት በቅተዋል፡፡ የለውጥ እንቅስቃሴንና መሥዋዕትነትን ስናስታውስ በግንባር ቀደም የምንዘክራቸው፥ የ1953ቱን ታህሣሥ ጀግኖች እነመንግሥቱ ንዋይንና የ1961ዱን ታህሣሥ ጀግኖች እነጥላሁን ግዛውን ነው፡፡ አንዱ በስቅላት ሌላው በጥይት ህይወታቸው አልፏል፡፡ ግድያው የተፈፀመባቸው ለኢትዮጵያ ሕዝብ የዴሞክራሲ መብት ሲባል በተነሱበት ዓላማ ግንባር ቀደም ሆነው በመቆማቸው ነበር፡፡ የታህሣሣውያን ለውጥ ፈላጊዎች ግንባር ቀደም መሥዋዕትነት ግን ተዳፍኖ ሳይቀር ውስጥ ውስጡን ሲቀጣጠል ቆይቶ፥ የየካቲቱን 66 ዓም ሕዝባዊ አመፅ አስከተለ፡፡ በየትኛውም ሀገር ለሚከሰተው ሕዝባዊ አመፅ የግንባር ቀደሙን ሚና የሚጫወቱት በጣም ጥቂት ተራማጅ ምሁራንና ነቅተው የተቆጩ ሀገር-ወዳዶች እንደመሆናቸው የኢትዮጵያ ተራማጅ ወጣቶችና ሀገር ወዳዶች ይህንን ሚና መጫወታቸው፥ የታሪክ ሂደትን የተከተለ ነበር፡፡ ታዲያ ወርሃ ታህሣሥን

Ethiopia will prevail !

EthioLion



የምናስታውሰው ሰማዕታቱን ዘክሮ ለማለፍ ብቻ ሳይሆን፥ ዛሬ የእነርሱን ታሪካዊ ገድልና መስዕዋታዊ ጀግንነት ለማንኳሰስ የሚጥሩትን ክፍሎች፥ ተው ይቅርባቸሁ፥ ደግ አይደለም፥ ያለፉትን ጀግኖች ሰማዕታት ኢትዮጵያውያን ታሪክ አትበርዙ፥ ታሪክን መበረዝ መመረዝ ሀገርንና ትውልድን ይጎዳል እንጅ ጠቀሜታ የለውም ለማለትም ጭምር ነው።

ምንም እንኳ የመከራ ገመዷ ገና ያልተበጠሰላት ቢሆንም ለሀገራችን ኢትዮጵያ ነፃነትና ደህንነት፥ ዕድገትና ብልፅግና፥ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓትና ፍትኅ-ርትዕ ሲባል አንድን ትውልድ የመተረ መሥዋዕት ተከፍሏል። የወዳጅ ጠላት የበዛባት ሀገር በመሆኗ ግን እስከዛሬ ድረስ ከመከራዋ ልትላቀቅ አልቻለችም። በተለይ ዛሬ ከጉያዋ የተፈለፈሉ እኩይ ዜጎቿ ከታሪካዊ ባዕዳን ጠላቶቿ ጋር በመመሳጠር፥ ልጆቿ ተስማምተው እንዳይኖሩ በርትተው በመሥራት ላይ ይገኛሉ። መልማቷ ቀርቶ መጥፋቷ እየተፋጠነባት ያለችውን ሀገር ለማዳን፥ ሌሎች አዳዲስ ታህሣሣውያን እንዲፈጠሩ የግድ ይላል። በአዲስ ራዕይ ለአዲስ መስዋዕት የተዘጋጀ ሀገር ወዳድ ትውልድ የማግኘቱ ጉዳይ ከሁሉ በፊት እንደሚያስፈልግ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከተገነዘበው ውሎ አድሯል። የተሰዋን ትውልድ ታሪክ እያቆሸሹ ግን ተተኪ ጀግና ትውልድ ለማፍራት ያስቸግራል። ኢትዮጵያ ሀገራችን እንደ ሀገር ሰማዕታት ጀግኖቿን ማክበር፥ ማወደስና መቀደስ ግዴታዋ ነው። የተሰዋን ትውልድ ታሪክ እየረገሙ፥ የተሰራውን መልካም ተግባር እያጠፉ፥ አኩሪ ባኅልን እያረከሱ፥ የነገን ብሩኅ ተስፋን አንግቦ የሚወጣን ተተኪ ትውልድ ማፍራት ከቶ የሚቻል አይሆንም። ስለ ኢትዮጵያ የወደፊት ብሩኅ ተስፋ የሚያስብ ዜጋ ሁሉ፥ ያለፈውን አኩሪ ታሪክና ጀግና እያከበረ ሀገሩን የሚያስከብር ትውልድ መተካት ግዴታውና የዜግነት ተልዕኮው መሆኑን ሊረዳው ይገባል። ሀገር እየጠፋች ነው ሲባል የቆዳ ስፋቷን እያጨረማመቱ ማውደም ብቻ ሳይሆን፥ የዜጎቿን ታሪክና ባኅል፥ ዕምነትና ዕሴትንም ጭምር ማጥፋት ማለት ነው። እነጥላሁን ግዛው የሥርዓቱ ጥይት ሰለባ እንዲሆኑ ካበቃቸው ምክንያት አንዱ፥ የኢትዮጵያ አኩሪ ታሪክና ባኅል በውጭ አልባሌ ባኅል መበረዝ የለበትም ብለው በመከራከራቸው ነበር።

የአንድ ሀገር የኅልውና ጥፋት የሚጀምረው ያንን ሀገር ሀገር አድርገው ካቆዩት መልካም መሠረታዊ ጉዳዮች፥ ማለት ታሪክ፥ ባኅል፥ የሕዝብ ዕሴትና ዕምነት ሲጠቁና ሲዋረዱ መሆኑን የተረዱ ታህሣሣውያን ጀግኖች እንደነበሩ አኩሪ ታሪካቸው ይመሰክርላቸዋል። የኢትዮጵያን እንደ ሀገር መቀጠል አጥብቀው የማይሹ የሀገራችን የውስጥና የውጭ ጠላቶች ከሁሉ አስቀድመው ሀገር ወዳዶችን የሚያጠፉትም ለዚሁ ነው። ሀገርን ለማጥፋት መጀመሪያ አርበኛውን የማጥፋት ዘዴ የተወረሰው፥ ከቅኝ ገዥዎች መሆኑን ስለምንረዳ፥ ዛሬ በባዕዳን አማካኝነት ወያኔዎቹ የሚያደርጉት ሀገርን የማጥፋት ሂደት እንደ ዱብ ዕዳ የወረደ ነው አንልም። አሁን ሀገራችን የደረሰባት የጥፋት ዘመቻ እንዲያው በድንገት የደረሰ ግብታዊ ክስተት ሳይሆን፥ የውጭ ጠላቶቿ ከውስጥ ከሃድያን ጋር በመተባበር ለረዥም ጊዜ ሲጠነስሱት የቆዩት ሴራ ነው። ይህንን ሴራ በየጊዜው ነቅተው እየተከታተሉ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ሲያሳውቁ የነበሩ ኢትዮጵያውያን ተራማጅ ኃይሎችና ሌሎች


Ethiopia will prevail !

EthioLion


ሀገር ወዳድ ዜጎች ስሚ ሳያገኙ ቀሩ:: ብዙዎቹም ተገደሉ፤ ጠፉ:: ሰዎች በጠፉበት ሀገር ቤቱም ወና በመሆኑ፥ ተከላካይ ጀግና ስላላጋጠማቸው፥ በባዕድ ድጋፍና መሳሪያ እየተጠቀሙ ዓላማቸውን አከናወኑ:: የታህሣሣውያንና የየካቲታውያን ጀግኖች ዓላማ፥ በይዘትም ይሁን በራዕይ፥ አንድ ስለነበር፥ ለሀገራቸውና ለሕዝባቸው ነፃነት፥ እኩልነትና አንድነት፥ እድገትና ብልፅግና ከማሳካት በቀር ሌላ ኃሳብ አልነበራቸውም:: ወቅታዊውን የሀገሪቱ ሁኔታ ለመለወጥ ግን ሌሎች ታህሣሣውያንም ሆኑ የካቲታውያን መፈጠራቸው የማይቀር መሆኑ ባይዘነጋም፥ ጠቅላላ የሕዝብ አመፅ መነሳቱ ደግሞ እንደዚሁ አይቀሬ ነው:: ሕዝባዊ አመፅ ሲመጣ በአንድ ሀገር ላይ የሰፈነውን አምባገነን ሥርዓት ድምጥማጡን አጥፍቶ ሀገሪቱን ከጥፋት ለማዳን ፍቱን መድኀኒት መሆኑ የካቲት ስድሳ ስድስትን ማስታወሱ ብቻ ይበቃል::

የዓለም ሕዝቦች ታሪክና ሥልጣኔ አሁን ካለበት ደረጃ የደረሰው፥ ለሥልጣኔያቸውም ሆነ ለታሪካቸው መሠረትና መነሻ ስለነበረው ነው:: መስራቾቹ በጀመሩት ላይ ተመርኩዘው ተተኪዎቹ እየገነቡት ይቀጥላሉ:: መሠረቱን እያሰፉና እያጠነከሩ ሀገርን ማሳደግና ማልማት የማንኛውም ሀገር ወዳድ ዜጋ ፍላጎት መሆኑ ነው ለሚቀጥለው ተተኪው ትውልድ እንደ መልካም አርዓያ ሆኖ ሊያገለግል የሚችለው:: ሀገርን የማሳደግና የመገንባት ኃላፊነት የሚወሰነው በአንድ ትውልድ ብቻ ሳይሆን በቀጣይነት ለሚመጡ ተከታታይ ትውልዶችም ጭምር ነው:: ይህ ሲባል ግን ተከታታይ ትውልዶች፥ ከሁሉ በፊት ለሀገራቸውና ለሕዝባቸው ታማኞች ሆኖ መገኘት መሠረታዊ መሆኑን ሁሉም ሊገነዘበው የሚገባ ነው:: የሀገርና የወገን ፍቅር፥ በፅናት ላይ የተመሠረተ ታማኝነት ከሌለው፥ የሀገር ግንባታ በድቡሽት ላይ እንደተሰራ ቤት ፍርክስክሱ ይወጣል:: ለሀገርና ለሕዝብ የሚኖር ታማኝነትን የሚተካው የለም:: በኢትዮጵያ ሀገራችን የፖለቲካ ታሪክ፥ የሀገሪቱ መሪዎችና የፖለቲካ ተዋናዮች ከሁሉ በፊት የሕዝብና የሀገር ታማኞች ባለመሆናቸው፥ ዘወትር ሀገራችን ለባዕዳን ጠላቶቿ እየተጋለጠች ቆይታለች:: በተለይም በቅርብ ጊዜ የመጡት የሀገርና የፖለቲካ መሪዎች፥ ከራሳቸው ሕዝብ ይልቅ ባዕዳንን ስለሚያምኑ የሕዝብን ፍቅርና ተዓማኒነት ፈፅሞ ሊያገኙ አልቻሉም:: ይህም በመሆኑ ሀገራችን ብዙ ጊዜ ዕውነተኛ ወዳጆቿንና ጠላቶቿን መለየት እማትችልበት ደረጃ እንድትደርስ አድርገዋታል:: የታህሣሥ መንፈስና ዓላማ ጥሏቸው የሄደው ሁለት ታላቅ ትዝታዎች አሉ:: አንደኛው ጥርጣሬ ውስጥ ሊገባ የማይችለው የሕዝብ ታማኝነት ሲሆን፥ ሁለተኛው በዓላማ ፅናት ላይ የተመሠረተ መሥዋዕትነት ናቸው:: የሕዝብ ታማኝነትን አንግቦና ከባድ መሥዋዕትንም እየከፈለ የሚታገልን ትውልድና ድርጅትን ታሪክ ለመንቀፍና ለማንኳሰስ የሚሞክር የሞራል ሥልጣን ሊኖረው የሚችል ግለሰብም ይሁን ተቋም አለ ተብሎ አይታሰብም:: ካለም ከሐቅ ጋር የተጣላና የማንነት ችግር ያለበት መሆን አለበት:: ለሕዝብ ነፃነት፥ ለሀገር አንድነት፥ ለዲሞክራሲያዊ መብት፥ ለዜጎች እኩልነትና ለህግ የበላይነት እታገላለሁ ብሎ የተነሳ ማንኛውም ድርጅትም ይሁን የድርጅት አባል፥ ሦስት ነገሮችን መሠረት አድርጎ ሊነሳ ይገባዋል:: እነርሱም፥ ለሚታገልለት ሕዝብ ሊኖረው የሚገባ ፍቅር፥ ታማኝነትና ለመሥዋዕት ዝግጁነት ናቸው:: በነኝህ መሠረቶች ላይ ተነስቶ ዓላማውን ከግቡ ለማድረስ ሲታገል፥ የሕዝብን


Ethiopia will prevail !

EthioLion


ሙሉ ድጋፍ፥ ፅኑ ተዓማኒነትና ያልተቋረጠ ትብብርና ተሳትፎ ያገኛል። የሕዝቡን የመጨረሻ ድል ለማስመዝገብ ደግሞ አይበገሬነትን የተላበሰ የዓላማ ፅናት አንግቦ ትግሉን መቀጠል አለበት። የትግል መርዘምና ውስብስብነት፥ የሚጠይቀውም መሥዋዕትነት እንዳለ ሆኖ፥ ሁሉንም እንደአመጣጡ ችሎና ተቋቁሞ መገኘት የኢትዮጵያውያን ታጋዮች ልዩ ባኅርያቸውና መታወቂያቸው መሆኑን እንኳን ወዳጅ ጠላትም የማይክደው ሐቅ ነው። ለዚህም ነው የሰማዕታቱ ህይወት ህያው ሆኖ የቀጠለው። ይህ ህያው ሆኖ የቀጠለው ትግል በበኩሉ ሽንፈትን ለመቀበል የማይከጅለውና የማይቀበለውም ለዚህ ነው። ምክንያቱም፥ ለዚህ ኃይል፥ የሽንፈት ትርጉሙ ዓላማን ሸጦ፥ በውቅታዊ ሁኔታዎች ተወናብዶ፥ ለባለሥልጣን ተንበርክኮ፥ የኢትዮጵያን ሕዝብ ክዶ፥ ተሽመድምዶና ተልፈስፍሶ ለአምባገነኖች ተዋርዶ ሲገዛ ነው። እየተገዙ መታገል የሚለው ቋንቋ በእርሱ መዝገበ-ቃላት ውስጥ አይገኝም። የዚህ ትርጉም አገላለጽ በኢትዮጵያ የፖለቲካ መልክዓ-ምድር ውስጥ የፖለቲካ ትግል እናካሂዳለን ብለው የቀዩትን ሆነ አሁንም እንታገላለን የሚሉትን በሁለት ጎራ ይመድባቸዋል። በመሠረቱ ይህ ምድብ የመጣው በሁለቱ መካከል ከመጀመሪያውኑ አንስቶ የባኅርይና የአመለካከት ልዩነት በመኖሩ ነው ማለት ይቻላል። ይኸውም የፓለቲካ ሥልጣን አያያዝ አቋም ነው። በአይበገሬነት ሳይሸነፍ ትግልን የቀጠለው ኢትዮጵያዊ ኃይል፥ የፖለቲካ ሥልጣንን የሚያየው ከጠቅላላው የኢትዮጵያ ሕዝብ የሥልጣን ልዕልና አኳያ ነው።

ዴሞክራሲያዊ የሆነ የሕዝባዊ መንግሥት ሥልጣን ዕውን ሊሆን የሚችለውና የሚገባው፥ የሕዝብን ሙሉ ተሳትፎ መሠረት ባደረገ የዴሞክራሲያዊ ሂደት ነው። የአንድ ሀገር ሕዝብ የራሱ ዕድል ወሳኝና የሕይወቱ ባላቤት መሆኑ ከታመነ፥ የመንግሥትንም ሥልጣን እርሱ በቀጥታ በመረጣቸው እንደራሴዎቹ አማካኝነት ሊመሠርት የሚችለው እርሱ ነው። ይህ መሠረታዊ ዕምነት ሥልጣንን በአቋራጭ መንገድ እንይዛለን ወይም በሆነው አጋጣሚ ሥልጣን ከያዘ አምባገነን ጋር ተዳብለን የሥልጣን ተካፋይ የምንሆንበት ዕድል ይፈጠርልናል ከሚሉት ክፍሎች ጋር የሰማይና የምድር ርቀት ያህል ልዩነት አለው። ይህ ክፍል ስለ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ መብትም ሆነ ነፃነት፥ ስለ ሀገር ብልፅግናም ይሁን ዕድገት ደንታ ሊኖረው ከቶ አይችልም። የዘወትር አጀንዳውም ምንጊዜም ቢሆን ወደ ሥልጣን በረንዳ የሚቀርብበትን ዘዴ ማውጠንጠን ብቻ ይሆናል። ይህ ባኅርዩና ተፈጥሮው የዓላማ ፅናትም ይሁን የሕዝብ አመኔታ እንዲኖረው አያደርገውም። ዛሬ በሀገራችን ያለው የፖለቲካ ተዋናይ የኃይል አሰላለፍ በነኝህ ሁለት ፈርጆች ተከፍሎ በመተራመስ ላይ ይገኛል። ይህም ማለት፥ አንደኛው ማንኛውንም አምባገነን ሥርዓት እየተቃወመ በዓላማ ፅናት የሚታገለው ሲሆን፥ ሁለተኛው ደግሞ በሆነው ዘዴ ወደ ሥልጣን ኮርቻ የሚፈናጠጥበትን ሁሉ ለማድረግ የሚተረማመሰው ነው። ለዚህም ይመስላል ወቅታዊው የሀገራችን ፖለቲካዊ ሕይወት እንደ አይጠ-መጎጥ በጨለማ ዳፍንት ውስጥ ገብቶ የሚደናበረው። ይህም በመሆኑ ነው የሀገራችንን የፖለቲካ ችግር ለመፍታት በሁሉም አቅጣጫ ሲገመገም መላ-ቅጡ የጠፋ የሚመስለው። በአሁኑ ወቅት የሀገሩ ችግር የማያሳስበው፥ ውርደቱ የማያቃጥለው፥ ችግሩ የማያንገበግበው ኢትዮጵያዊ ዜጋ ይኖራል


Ethiopia will prevail !

ብሎ ለማሰብ ያስቸግራል፡፡ ስለዚህም ሁሉም የኅብረተስብ አባል ከሞላ ጎደል የሀገሩን ችግር አስመልክቶ ተመሳሳይ አመለካከት አለው ማለት ከተቻለ፥ በመፍትሄ አፈላለጉ ላይ ለምን ተቀራራቢ ግንዛቤ ለማግኘት አልተቻለውም የሚለውን ጥያቄ ጠይቆ መልስ ለማግኘት እንደማይጣጣር አስቸጋሪ ሆኗል፡፡ የሀገሩን ሰርዶ በሀገሩ በሬ እንደሚባለው፥ የሀገራችንን ችግር እኛው ራሳችን ካልፈታነው ማንስ ሊፈታልን ይችላል? ሰማዕታቱን እየኮነን፥ ሀገር ወዳድ ምሁራንን እያወገዝ፥ የሕሊና እስረኞችን እየረሳን፥ ታጋዮቹን እየረገምን፥ አርበኞችን እያዋረድን፥ ጀግኖቻችንን እየቀበርን እንዴትስ ብለን የሀገር መሪ እናፈራለን? ኢትዮጵያ፥ ወያኔዎች ሀሰትን አንግሰው እንደሚሉት፥ የአንድ መቶ ዓመት ታሪክ ያላት ሀገር ሳትሆን በሽህ የሚቆጠሩ ዘመናት ታሪክ ያስመዘገበች ምድር ነች፡፡ ምንም እንኳ የአያሌ ዘመን ባለታሪክ መሆን ብቻ ከችግራችን ሊያላቅቀን ይችላል የሚል ብዥታ ባይኖርም፥ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣው ተመክሮና በራስ የመተማመን ባኅርያችን የራሳችንን ችግር ለመፍታት በቂ ችሎታና ዕውቀት ባስገኘልን ነበር፡፡ ታሪካችን እንዳስተማረን ቢሆንማ ኖሮ፥ ሀገራችን ኢትዮጵያ የራሳቸውን መንግሥት መሥርተው ራሳቸውን ሲያስተዳድሩ ከነበሩ ጥንታውያን ነፃ ሀገሮች መካከል አንዷ እንደነበረች እንረዳለን፡፡ ያም ሆኖ ደግሞ፥ መንግሥቷን መሥርታ ወደልማቷና ሥልጣኔዋ አተኩራ ወደፊት እንዳትገሰግስ፥ የውጭ ወራሪና የሀገር ውስጥ የርስ በርስ ብጥብጥ በአብዛኛው ዘመኗ እድል አልሰጣትም፡፡ ለረዥም ጊዜ ሀገሪቱ ሠላምና መረጋጋትን አግኝታ፥ ሌላው ቢቀር፥ ዜጎቿን መመገብ እንኳ አልቻለችም፡፡ ይኸ የታሪክ ሐቅ የማይካድ ቢሆንም፥ በዚህ ምክንያት ዛሬም እንደ ትላንቱ የምግብ እርዳታ ለማግኘት የባዕዳንን እጅ ለማየት እየተገደደች ነው፡፡ ለድህነታችን፥ ለችግራችን፥ ለርሀብተኝነታቸን፥ ወደኋላ ለመቅረታችን፥ ዋናዎቹ ምክንያቶች፥ በየጊዜው በውጭ ኃይሎች መወረራችንና የእርስ በእርስ ጦርነቶቻችን ናቸው ብለን፥ ለማጠየቂያ ልንጠቀምባቸው የሚገባን አይመስለንም፡፡ የማንኛውም ኅብረተስብ ጨቋኝ መሪዎችንና የቅኝ ገዥዎችን ካልታገለ ነፃ እንደማይወጣ ከራሱ ከተጨቋኙ የበለጠ የሚያውቅለት አይገኝም፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ በየጊዜው ባዕዳን ወራሪዎቹን እያሸነፈ ቢያባርርም፥ የውስጥ አምባገነኖችን እያስወገደ፥ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን ለመመስረት ግን እስካሁን አልተሳካለትም፡፡ ይህንን ሐቅ አበከረው የተረዱ ባለራዕዮች፥ ሀገር ወዳድ ምሁራንና ተራማጅ ዜጎች የሀገሪቱን ችግር ለመቅረፍ በየጊዜው እየተነሱ ባደረጉት ሙከራ የእሳት እራት እየሆኑ ቀርተዋል፡፡ የሀገሪቱን ወደኋላ መቅረት ብቻ ሳይሆን የምታመራበትንም አደገኛ የጥፋት አቅጣጫ ጭምር በመጠቆም፥ በድፍረት አምባገነን መሪዎችን በመጋፈጥ ድምጻቸውን ያሰሙ ሁሉ፥ የሥርዓቱ ሰለባ እየሆኑ ቀርተዋል፡፡ ይህ ክስተት አሁንም እንደቀጠለ ነው፡፡ ከዚህ አዙሪት እንዴትና መቸ እንደሚወጣ የሀገሪቱ እንቆቅልሽ ብቻ ሳይሆን የሕዝቡም የዘወትር ሰቆቃና ምኅላ ሆኗል፡፡ የሰማዕታቱ ደምና የአርበኞቹ አፅምም የትዝብት መልዕክቱን ማስተላለፉን ቀጥሏል፡፡ ዕልፍ አዕላፍ የኅሊና እስረኞችም ኤሎሄአቸውን ማሰማት አላቆሙም፡፡ ፍትኅ-ርትዕ በጠፋበት፥ ግፍና በደል በነገሰበት፥ ረሀብ፥ በሽታና ድህነት በተስፋፋበት፥ ብሔራዊ ጥቃትና ውርደት ሥር በሰደደበት ሀገር፤ ብዙው ዜጋ ሀገሩን እየለቀቀ ለመውጣት

EthioLion



በተሰለፈበት ሀገር፥ ሰላምና መረጋጋት ይገኛል ብለው የሚመሙ ካሉ፥ እራሳቸውን እያታለሉ የሚኖሩ ብቻ ናቸው። በተለይማ አንድ ሀገር፥ ልክ በነዳጅ እንደተነከረ ጨርቅ ዓይነት ሆና በምትመሰልበት ሁኔታ፥ እንደልቤ እየገዛሁ እቀጥላለሁ የሚል አምባገነን ጤናማ አዕምሮ አለው ለማለት ያስቸግራል። አጥፍቼ ልጥፋ ካላለ በስተቀር!

ይህ የወቅቱ የዘረኛ ሥርዓትን አራማጅ ቡድን፥ ከራሱ ዕይታ አንፃር፥ የሀገሪቱን ሁኔታ ለመገምገም የሚያስችለው ዕውቅት እንዳለው ለማመን ይፈልጋል። ከዚህ አመለካከት በመነሳትም፥ ከአንድ የቀቢፀ-ተስፋ ድምዳሜ ለመድረስ ይከጅላል። ይኸውም የአካባቢና የዓለም አቀፍ ሁኔታዎች በጅተውኛል፤ የሀገር ቤቱንም ሁኔታ ተቆጣጥሬዋለሁ፤ ተቃዋሚ ኃይሉንም ከፋፍያለሁ፤ ለምዕራባውያን ያለኝን ተገዥነት ስለአረጋገጥኩላቸው የእነርሱን እርዳታና ትብብር በማያቋርጥ መልኩ አገኛለሁ፤ የአፍሪካ አህጉርም አፈ-ቀላጤ ሆኛለሁ፤ ከወርቅ የተሰራሁ በመሆኔ፥ የትግራይን ወርቃማ ዘመን አረጋግጫለሁ፤ ሁሉ በእጄ ሁሉ በደጄ ሆኖልኛል ከሚል የሥነ አዕምሮ ቅዠት ውስጥ ገብቶ ይዋኛል። ይህ ቅዠቱም፥ ላልተወሰነ ጊዜ የኢትዮጵያን ሕዝብ፥ እንደ ገል ቀጥቅጬ፥ እንደ ሰም አቅልጨ እገዛለሁ ብሎ እራሱን በማታለል ላይ ያለ ቡድን ነው። ይህ የውጥረት፥ የእብጠትና የትዕቢት አነጋገር፥ በዘመናት የተነሱ አምባገነኖች ሁሉ ሲለፍፉት የነበረ በመሆኑ ማንንም ሊያስገርም አይችልም። ትላንትናም የደርግ አለቆች፥ ተፈጥሮን ተቆጣጥረናል ሲሉ እንደነበረ የቅርብ ትዝታ ነው። እነርሱ ግን እንኳንስ ተፈጥሮን ቀርቶ እራሳቸውንም መቆጣጠር ተስኗቸው ሕዝባቸውን ከድተው ሀገራቸውን አጋልጠው ነው የጠፉት። የዛሬዎቹም ከህዲዎች በተመሳሳይ አቅጣጫ እየነጎዱ ናቸው። ይህን ተመሳሳይ የመጥፋት ጉዞ ማንም ሊያስቀረው ስለማይችል፥ በድንቁርና የተወጠረው ትዕቢታቸው ከመጥፋት አያድናቸውም።

አምባገነኖች በመጨረሻ ዘመናቸው ጠፉም አልጠፉም፥ ሀገሪቱን የማዳን ኃላፊነትና ግዴታ ግን የሕዝቡና በዓላማው ፀንቶ የሚታገለው ኢትዮጵያዊው ኃይል ነው። ይህ ኃይል ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር እጅና ጓንት ሆኖ ትግሉን ከቀጠለ፥ የዘለዓማዊት ኢትዮጵያን ህልውና የማያረጋግጥበት አንዳችም ምክንያት አይኖርም። የታህሣሳውያን ሰማዕታት ዓላማናራዕይም ህያው ይሆናል። ቀደምት ሰማዕታት የቀደዱትን ፈር ተከትሎ በአይበገሬነት ትግሉን የቀጠለው ኃይል ዓላማው፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ የሥልጣኑ ባለቤት ሁኖ የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እንዲያገኝ በመሆኑ፥ ዓላማው ግቡን ሳይመታ ዝናሩን የሚፈታ አይሆንም። የወርሃ ታህሣስን ሰማዕታት ስንዘክር ህይወታቸው መና ሆኖ እንደማይቀር ለማረጋገጥም ጭምር ነው።

ትግላችን ይቀጥላል!!
ድል አድራጊ ሕዝብ ነው!!


Ethiopia will prevail !